IBO IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

# AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1
# AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1
# AMHARE A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1

Monday 19 May 2003 (morning)
Lundi 19 mai 2003 (matin)
Lunes 19 de mayo de 2003 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- Ne pas ouvrir cette épreuve avant d'y être autorisé.
- Rédiger un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d'orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.

## ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየትህን ስጥ(ስጪ)።

**1. (ሀ)**

ያዲሳባ መኳንንትና ሴት ወይዛዝርት ደግሞ ተያይተው የማያውቁ ይመስል ፤ ቤተክስርቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ወሬና መሳሳም ያበዛሉ ።አንዱ ይወጣል ። ሌላው ይገባል ። ቅዳሴ ገብተው እስቲወጡ ድረስ አስችሎት የሚቆይ የለም ።

አንድ ቀን ፤ ለገሐር ስንለምን ሁለት ባለመኪኖች ፤ “ይኸ ሕዝብ በሙሉ ለማኝ ሆነ ልበል?” አለ አንደኛው ፊቱን ኮሶ አስመስሎ ። “እኔን የሚያናድደኝ እኛን በመለመናቸው አይደለም ። አንድ ቀን አንድ አሜሪካዊ ፤‘የሀገር ለማኞች መንገድ ከለከሉኝ’ ካለኝ ወዲህ አሜሪካዊውን ሳየው አፍራለሁ ። ለማኞች ሳይም እሸማቀቃለሁ” አለው ።

አቅኚ ለማኞች ፤ እኛን መጤዎችን አይወዱንም ። “እናንተ ከመጣችሁ ወዲህ ነው ያዲሳባ መኳንንት ልቡ የጨከነና ለማኞችን መርዞ የጨላን ። ዱሮ ለማኝ ብርቅ ነበር ። ካንድ ብር በታች የሚመጸወት አልነበረም” ይሉናል ። ግን ዐልፎ ላቸው አላየሁም ። ከኛ እኩል ልመና ይንከራተታሉ ።

መንጋ ለማኝ ፤ ሰማይ ሲዞርበት ጊዜ በኛ ያሳብባል ። ላንዲት ፉርኖ የሚደረገው ግብግብ መፈጠርን ያስጠላል ። ዱሮ በኩሊነቴ አንድ ዘንቢል ለመሸከም ብዙ ኩሊ ግብግብ ይፈጥርና ይደባደብ እንደነበረው ዐይነት ነው ። እንዲያውም አዲሳባ ማር ቅጠሉ ብር ብር ይሳል ።

ንጉሡን ማማት በጥብቅ የተከለከለ ነው ። ባትወዳቸውም እወዳቸዋለሁ ማለት አለብህ ። አለበለዚያ ጆሮ ጠቢ ያሻውክብሃል ።

አንዱ ብልጥ በዚህ እንዴት እንደሚጠቀም ልንገርህ ። ምንም ገንዘብ ላይኖረው መጠጥ ቤት ይገባል ። ከዚያ አንዱን መኳንንት ጠጋ ብሎ ፤ “ጌታዬ ከሁሉ አብልጠው የሚወዱትን ዐውቃለሁ” ይላቸዋል ።

“ሐሰት! አታውቅም” ይሉታል ።
“እንወራረድ!” ይላቸዋል ።
“ሃምሳ ብር እስጥ!” ይሉታል ።

“ግድየለም ዐሥር ብር ይበቃል” ይላል አጅሬ ።

“መልካም” ይላሉ ።

“ከሁሉ አብልጠው የሚወዱ ጃንሆይን ነው” ይላቸዋል ። መቼም ካሥር ብር ሕይወት ይበልጥባቸዋልና ዐውቀው ይረታሉ ።

የጃንሆይ ነጭ ለባሽ ፣ እንዳገርህ ነጭ ለባሽ አይምሰልህ ። አንድ ነጭ ለባሽ ከበርቴዎችን ከበርቴ መስሎ ፣ ለማኙን ለማኝ መስሎ ፣ ተማሪውን ተማሪ መስሎ ይጠጋል ። ዕብዱን ለመያዝ ዕብድ መስሎ ራቁቱን እየሔደ ነው ። አንድ ጥይት ሳይተኩስ ሺ ገድሎ የሚገባ ነው ።

ይህን ደብዳቤ አንብበህ ስትጨርስ ቅደደው ፤ አለበለዚያ መዘዝ ያመጣል ። ‘ያልጠረጠረ ተመነ ጠረ’ ተብሏልና ፣ በንዝህላልነት ከጅህ ካመለጠ ወዮልህ ። ጃንሆ ይ ነገርና ሰው አይንቁም ይባላል ። ሲቀጡ እስከ ሰባት ትውልድ ነው ። ለራሴ ፈርቼ እንዳይመስልህ ። እኔማ ከቤተ ክርስቲያን የወጣሁለት ባላፈርስም አፍርሻለሁ ። ጃንሆይ ፊት የተደበደብኩለት ባልሞትም ሞቻለሁ ።

ጃንሆይ ፡ በቁመት ካፍ የወደቀ ጥሬ ያክላሉ ። ጠድፍ ጠድፍ እሚያካክሉ አንጋቾች መካከል ስታያቸው ሕፃን ይመስላሉ ። ያ ሁሉ መኳንንት በዙሪያቸው ሲያዘጠዝጥ ያስገርማል ። ያስቅማል ።

የባሰ የሚያስገርም ደሞ ፣ ጃንሆይን ለማየት የሚደረገው ግፊያና ትንንቅ ፡ የፖሊሶች ዱላና ርግጫም አይደለም ። እንደ መልክአ ማርያም ፣ እንደ መልክአ ኢየሱስ ሁሉ መልክአ ኃይለሥላሴ ተደርሶላቸው ፣ ያዲሳባ ምዕመናን በትጋት ሲጸልዩበት ማየት ነው ይበልጥ የሚያስደንቅ ።

በቅዳሴውም ፣ በቅኔውም ፣ በጸሎቱም የጃንሆይ ስም ሺ ጊዜ ካልተጠራ ቅዳሴውም ቅዳሴ አይደለም ፤ ቅኔውም ቅኔ አይደለም ።

አውግቸው ተረፈ፤ <u>ወይ አዲስ አበባ</u>፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1979::

ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ምን ይመስልሀል?

የዋናውን ገፀባህሪ አቀራረብና አላማ አብራራ::

የፅሁፉን አስቂኝ አቀራረብ ግለፅ::

**1. ለ**

**ተረቶች**

የጉባኤ ፈርጦች:
የሸንጎ አድማቂዎች
የአፈርሳታ ወጎች
የአገር አውጋር ኮከብ የየታሪኩ አምዶች:
የሚሥጢራት መፍቻ፣ የኑሮ ፋናዎች
የማይናወጡ...
የማይለወጡ....
የዘመን መልሕቆች
ሲኖሩ፣ ማይኖሩ...
ሲታጡ፣ ሚያኮሩ
እስቲሞቱ ድረስ ታይተው ሚታለፉ:
በሱሰኞች ተራ አለአባት ሚጻፉ፡
እነሱን አያርገኝ....
የጥበብ ቅምጦች...
የፈጠራ ሰዎች::

**አረጋሽ ሠይፉ : <u>እኛ: 170 ግጥሞች</u>፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1990::**

**የግጥሙ ዋና ጭብጥ ምንድነው?**

**በግጥሙ ውስጥ የፈጠራ ሰዎች እንደምን ቀርበዋል?**

**ገጣሚዋ በአንባቢው አመለከከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመችባቸው ቴክኒኮች ላይ አስተያየት ስጥ::**